# የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የሰው ልጆች ከሥርዓተ ምህዳር የሚያገኙዋቸው ልዩ ልዩ ጥቅሞች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህም አገልግሎቶች በዋናነት በአራት የሚከፈሉ ሲሆን እነዚህም፡-

1) የአገልግሎት አቅርቦት፡- የምግብ፣ የውሃ፣ የጣውላ፣ የማገዶ አቅርቦት የመሳሰሉት፤
2) የቁጥጥር አገልግሎቶች፡- የአየር ጥራት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና የጎርፍ አደጋ መከላከል የመሳሰሉት፤
3) የባህል አገልግሎቶች፡- ለመዝናኛ ፣ለቱሪዝም እና ለትምህርት የመሳሰሉት፤
4) የድጋፍ አገልግሎቶች፡- የአፈር መፈጠር እና የአፈር ንጥረ-ነገር ዑደት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከሥርዓተ-ምህዳር የሚገኝ ማንኛውም አገልግሎት ዓይነት፣ ጥራት እና መጠን በግለሰቦች እና ማህበረሰቦች የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ውሳኔዎች የሚወሰን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ ሥርዓተ-ምህዳሮች የሚሰጡት አገልግሎት ተፈጥሮአዊ በሆነ እና በሰዎች ጣልቃ ገብነት ምክንያት በከፍተኛ ጫና ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እ.አ.አ በ 2000 ዓ.ም በሚሊኒየም ኤኮሲስተም ግምገማ ጥናት መሰረት ከ60% በላይ የሚሆነው የዓለም ሥርዓተ-ምህዳሮች ዘላቂነታቸው ባልተረጋገጠ መንገድ ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሆነ እንዲሁም በተፈጥሮ ማገገም ከሚችሉት በላይ በፍጥነት እየተመናመኑ መሆኑን አመላክቷል፡፡ እንደ ግብርና ምርት ያሉ አንዳንድ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ሲጨመሩ ሌሎች አብዛኛዎቹ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች በማሽቆልቆል ላይ ይገኛሉ፡፡ የግብርና ምርታማነት መጨመር ምክንያትም በአብዛኛው በሌሎች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች በተለይም በብዝሃ ህይወት ፣በአየር፣ በአፈር እና በውሃ ጥራት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር የተገኘ ውጤት ነው፡፡

ከዚህም በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄደው የህዝብ ቁጥር እና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን የመቀነስ እድልን ጠባብ እንደሚያደርገው ይገመታል፡፡ ሆኖም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ዋጋ ላይ የተፈጠረው ሳይንሳዊ ግንዛቤ ማደግ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ለኢኮኖሚ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ በፖሊሲዎችና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እየተንፀባረቀ ይገኛል፡፡

## 2. የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ክፍያ ፅንሰ ሀሳብ

የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ማለት የሥርዓተ-ምህዳር ተጠቃሚዎች ለሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች አቅራቢዎች ክፍያ የሚፈፀምበት አሰራር ነው። በዚህም መሰረት ለተረጋገጠ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ለማግኘት ለመሬት ወይም ለሌሎች የተፈጥሮ ሃብት ባለቤቶች ወይም አስተዳዳሪዎች አቅርቦታቸውን ሊያሳድጉ ለሚችሉ እርምጃዎች ክፍያዎች የሚፈፀምበት አሰራር ነው።

ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ክፍያ በስተጀርባ ያለው መሰረታዊ ሃሳብ እንደ ማንኛውም አገልግሎት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሻሻል ወይም በዘላቂነት እንዲቀጥል አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ አካላት በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ክፍያ የሚፈፀምበት አሰራር ነው። ይህም ቀደም ሲል ዋጋ ባልተተመነላቸው የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ላይ ዋጋ ለመተን እድል የሚሰጥ ሲሆን ይህም አገልግሎቶቹን ወደ ሰፊው ኢኮኖሚ የሚያካትት ይሆናል።

## 3. የረቂቅ አዋጁ አስፈላጊነት

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 545/2016 ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት አንዱ መሰረት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ አገልግሎት ክፍያ ወይም የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እና አተገባበሩን መከታተልና መቆጣጠር እንደሆነ በደንቡ አንቀፅ 5 (13) ላይ ተደንግጓል። በሀገራችን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አሰራርን የተመለከተ የህግ ማዕቀፍ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የክፍያ አሰራሩን አተገባበር የሚከታተል ተቋም ባለመኖሩ ወጥ ባልሆነ አሰራር በተለያዩ አካላት ሲተገበር ቆይቷል። በመሆኑም የሀገራችንን ሥርዓተ ምህዳር በዘላቂነት ለማስተዳደር የፌደራል እና የክልል ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ልዩ ፍላጎት እና ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4. የረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ሂደት እና የተወሰዱ ግብዓቶች

ረቂቅ አዋጁ አሳታፊ በሆነ ሁኔታ የተዘጋጀ ሲሆን ከረቂቅ ዝግጅቱ ጀምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ላይ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የሚመለከታቸው የፌደራል መንግስት ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የክልል የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ ሀላፊዎች እና ባለሙያዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሳተፉባቸው በርካታ የምክክር ዓውደ-ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን ከምክክር መድረኮቹ የተገኙ ግብዓቶች በረቂቁ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ላይ የዓለም ባንክ የቴክኒክ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን ረቂቅ አዋጁ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ለፍትህ ሚኒስትር ተልኮ በረቂቁ ላይ ከሚኒስቴሩ የተሰጡ አስተያየቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 5. የረቂቅ አዋጁ ይዘት

ረቂቅ አዋጁ በሰባት ክፍሎች እና ሀያ አንቀፆች ይዞ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በረቂቁ የተካተቱ ጉዳዮች እና መነሻ ምክንያቶች በሚከተለው መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### 5.1 የአዋጁ መግቢያ

በረቂቅ አዋጁ መግቢያ ኢትዮጵያ ብዝሃነት ባላቸው ሥርዓተ ምህዳሮች የበለፀገች እና እነዚህ ሥርዓተ ምህዳሮች በሀገራዊ የልማት ጥረቶች ላይ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ አስተዋፅኦ ማሳደግ ማስፈለጉ፤ እነዚህ ሥርዓተ-ምህዳሮች ዘላቂ ባልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት በከፍተኛ ጫና ውስጥ በመሆናቸው ሥርዓተ ምህዳርን በዘላቂነት ለማስተዳደር የሚያስችል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን፤ የፌደራል እና የክልል ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ልዩ ፍላጎት እና ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### 5.2 ትርጓሜ

ግልጸኝነት የሚፈልጉ እና በአዋጁ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ወይም ሀረጋት በአንቀፅ 2 እንዲተረጎሙ ተደርጓል፡፡

### 5.3 የአዋጁ የተፈፃሚነት ወሰን

አዋጁ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች፣ አደራዳሪዎች እና በዚህ አዋጅ አባሪ 1 ስር በተዘረዘሩት የሥርዓተምህዳር አገልግሎት አይነቶች ላይ በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ላይ በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ተፈፃሚ እንደሆነ በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 3 ላይ ተመላክቷል፡፡ ረቂቅ አዋጁ በሁሉም የኢትየጰያ ግዛት ተፈፃሚ የሚሆነው የክልሎችን እንዲሁም የሌሎች የፌደራል የዘርፍ መስሪያቤቶች ህግ የማውጣት ሥልጣን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በአዋጁ የተቀመጡ መስፈርቶችን በማይቃረን መልኩ የአዋጁ ሀገራዊ አተገባበር ላይ ወጥነት እንዲፈጠር ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

### 5.4 የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መርሆዎች እና መልክዓ-ምድራዊ ሽፋን

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 4 የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አሰራሮች መከተል የሚኖርባቸውን መርሆዎች የሚዘረዝር ሲሆን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ ስምምነት በፍቃደኝነት የሚገቡ መሆኑ፤ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ክፍያውን በቀጥታ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ የሚከፍል መሆኑ፤ ክፍያ የሚፈፀመው አንድ የተወሰነ ሥርዓተ-ምህዳር ሁኔታን የማሻሻል እና የመጠበቅ አላማ ለሚያደርጉ የመሬት፣ የውሃና ሌሎች ሀብቶች አያያዝ ሥርዓቶች መሆኑ እና በአንድ አካባቢ ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን ሂደት አሉታዊ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ነው ፡፡

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 5 የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ በተለያዩ መልክዓ-ምድራዊ ሽፋንን (Spatial Scale) መሰረት አድርገው ሊዘጋጁ የሚችሉ ሲሆን አለም አቀፍ፣ ሀገር አቀፍ፣ የተፋሰስ ወይም በወረዳ ደረጃ ሊዘጋጁ እንደሚችሉ ተመላክቷል፡፡ ይህንንም በምሳሌ ለማስረዳት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

> **አለም አቀፍ-** ምሳሌ ሀገራት በአለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች መሰረት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የሚያካሂዷቸው የካርቦን ንግዶች ሊሆን ይችላል፡፡ በሀገራችን እየተተገበረ የሚገኘው ከደን መጨፍጨፍ እና ከደን መራቆት ምክንያት የሚመነጨውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ የሚተገበረው ፕሮጀክት (Reducing Emissions from Deforestation and Forest Degradation) ጥሩ ምሳሌ ሲሆን ይህም ሀገራት ከደን መጨፍጨፍ እና ከደን መራቆት ምክንያት የሚመነጨውን የሙቀት አማቂ ጋዝ

ለመቀነስ ለሚያከናውኗቸው የደን ልማት እና አጠባበቅ ስራዎች ድጋፍ የሚገኙበትን ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን በዚህም ለተረጋገጡ የደን መጨፍጨፍ ቅነሳ እና የካርቦን ልቀት ቅነሳ (Carbon Sequestration) ክፍያ የሚፈፀበት አሰራር ነው፡፡

**ሀገር አቀፍ** - ምሳሌ መንግስት አጠቃላይ ህዝቡን በመወከል አርሶ አደሮች በመሬት እና በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና አጠባበቅ ላይ በሚያከናውኗቸው ስራዎች ምክንያት አዲስ ለሚፈጠሩ ወይም ለሚሻሻሉ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ክፍያ የሚፈፀምበት ሁኔታ ነው፤

**ክልል አቀፍ**- ምሳሌ በአንድ ክልል የሚገኙ ነዋሪዎች በብዝሃ ሕይወት እና የዱር እንስሳት ሀብት አጠባበቅ ላይ በሚያከናውኗቸው ስራዎች ምክንያት ለሚሻሻሉ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ክፍያ የሚፈፀምበት ሁኔታ ነው፤

**ተፋሰስ ወይም ንዑስ ተፋሰስ**- ምሳሌ በታችኛው ተፋሰስ ላይ የሚገኙ የውሀ ተጠቃሚዎች ዘላቂ የውሀ አቅርቦትን ለማግኘት እንዲሁም የጎርፍ አደጋን ለመከላከል እንዲችሉ በላይኛው ተፋሰስ ለሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ስራዎች ክፍያ የሚፈፀምበት አሰራር ነው፤

**ወረዳ (local level)** - ምሳሌ የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች የአረንጓዴ ቦታዎችን ለመዝናኛነት እና ለብዝሃ-ህይወት ጥበቃ አገልግሎት ለማዋል በአካባቢ እንክብካቤ ላይ ለተሰማራ ተቋም ክፍያ የሚፅሙበት አሰራር ነው

## 5.5 ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 6 የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ቢያንስ አንድ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አላማ ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ታሳቢ ሊደረጉባቸው የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራል፡፡ በሌላ በኩል የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 7 ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ሊይዝ የሚገባቸውን ዝርዝር ጉዳዮችን ይደነግጋል፡፡

### 5.6 የአከፋፈል ሁኔታ፣ የፋይናንስ ምንጭ እና የጥቅም መጋራት

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 8 ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ስምምነት እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት ክፍያ ተፈፃሚ የሚሆነው ለተረጋገጡ ውጤቶች ብቻ እንደሆነ የክፍያ ዓይነቶቹም ውጤት ተኮር ወይም ግብዓትን መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚችል ተመላክቷል፡፡

የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ምንጮችን በተመለከተ ሶስት መንገዶች በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 9 ላይ የተመላከቱ ሲሆን እነዚህም መንግስት ህዝብን በመወከል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎትን ለማሳደግ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ የሚከፍልባቸው የመንግስት ክፍያ መርሃ ግብሮች፤ ግለሰቦች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት በቀጥታ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ክፍያ የሚፈፅሙበት እና በመንግስትና በግለሰብ ጥምረት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት ለየሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ክፍያ የሚፈፀምበት መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 10 በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሻጮች መካከል የሚደረግ የጥቅም መጋራት ታሳቢ ሊያደርግ የሚገባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

የጥቅም መጋራትን በተመለከተ የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 10 ማንኛውም የጥቅም መጋራት ስምምነቶች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ መካከል ከመፈረሙ አስቀድሞ መከናወን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም .ማንኛውም በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ መካከል የሚደረግ የጥቅም መጋራት ጉዳዮች በቅድሚያ ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ የሚገቡ ጉዳዮች በዝረዝር ተመላክተዋል፡፡

### 5.7 የአደራዳሪ ሚና እና ክትትል፣ ሪፖርት እና ማረጋገጥ

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 11 አደራዳሪ በሥርዓት ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ የሚኖሩትን ሚናዎች በግልፅ ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 12 የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበር የክትትል፣ የሪፖርት እና የማረጋገጥ ስራዎች የሚከናወኑበትን ሁኔታ በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡

### 5.8 የተቋማት ሚና

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 12 በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አተገባበር ላይ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑ ተቋማትን በመለየት የእያንዳንዱን ተቋም ሀላፊነታቸውን ዘርዝሮ አስቀምጧል። በዚህም መሰረት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የክልል ባለሥልጣን፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣የገንዘብ ሚኒስቴር እና የዘርፍ መስርያቤቶች ሀላፊነቶች በግልፅ በአዋጁ ተመላክቷል።

### 5.9 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 18 በአዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎች ያልተከበሩ እንደሆነ ባለስልጣኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነትን መሰረዝ እንደሚችል ይደነግጋል። በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ባለሥልጣኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነትን ሊሰርዝ የሚችልባቸውን ምክንያቶች በግልፅ ተመላክተዋል።

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 19 ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ እንደማይሆን የሚደነግግ ሲሆን ሆኖም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ እድሳት ወይም ማሻሻል የሚፈፀመው በዚህ አዋጅ መሰረት መሆኑ ተመላክቷል።

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 20 የሚንስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦች ሊያውጣ እንደሚችል እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ለአዋጁ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን እንደሚያወጣ ተመላክቷል።